## ቀስተደመና ሬድዮ ትችት

# ከቡናው ቀውስ እንዴት እንውጣ?

ግዙፍና ድንበር ዘለል በቡና ንግድ የተሰማሩ ኩባንያዎች ለድሃ ቡና አምራች ገበሬዎች የሚከፍሉት ዋጋ ባለፉት አምስት አመታት በሰባ በመቶ ቀንሱዋል። የሃገራችን ገበሬዎች የዛሬ አምስት አመት አንድ ኪሎ ቡና ወደውጭ ሲላክ እስከ አምስት ብር ከሃያ ሳንቲም ያገኙ ነበር። ዛሬ ለአንድ ኪሎ ቡና የሚያገኙት ሰማንያ አምስት ሳንቲም ብቻ ነው። ሃገሪቱ ወደ ውጭ የምትልከው ቡና ከመቀነስ ይልቅ ቢጨምርም ከዚህ ኤክስፖርት የምታገኘው ገቢ ከሁለት መቶ አምሳ ሰባት ሚልየን ወደ መቶ አርባ ዘጠኝ ሚልየን ወርዱዋል። በዚህ አመት ብቻ 110 ሚልየን ዶላር ኪሳራ ደርሱዋል።

ይህ ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የኑሮ ተስፋቸውን በቡና ምርትና ንግድ ላይ የመሰረቱትን ወደ አስራ አምስት ሚልዮን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያንን ይህ ነው የማይባል የኑሮና የህልውና ቀውስ ላይ ጥሉዋቸዋል። በመጭው አመት ሁለት አመት ከዚህ ቀውስ መውጫው ዘዴ የማይታያቸው የሃገራችን ገበሬዎች የቡና ተክላቸውን እየመነጠሩ አንዳንዶቹ በቆሎና ሌላ ለምግብ የሚሆን እህል መዝራት ጀምረዋል። ሌሎች ደግሞ ወደ ጫት ማምረት ተዛውረዋል። የሆነ ሆኖ ይህ እርምጃ ዛሬ ተወጥረው ለተያዙበት ችግር መፍትሄ ስለማይኖር ትላንት ኑሮዋቸውን በተደላደለ ሁኔታ አሸንፈው ይኖሩ የነበሩ የሃገራችን ገበሬዎች ዛሬ በባንክ እና በሌላ እዳ ተወጥረው ተይዘው ለህልውናቸው የእርዳታ እህል ላይ ለመተማመን ተገደዋል።

ይህ የቡና ቀውስ ከየት መጣ? ተጠቃሚዎቹስ እነማን ናቸው? ከቀውሱ እንዴት መውጣት ይቻላል?

መጀመሪያ ዋጋ ለምን ወደቀ? ላይ ላዩን ሲያዩት የቡና ዋጋ የወደቀው በአለም ገበያ ያለው አቅርቦት ከሚፈለገው በላይ ስምንት በመቶ ሆኖ በመገኘቱ ነው ተብሉዋል።

ይህ ትርፍ ምርት ታዲያ ለምን ገበያውን እንዲያጥለቀልቅ ተደረገ? ይህ የሆነበት ምክንያት ከግሎባላይዜሽንና ለምእራቡ አለም ብቻ እንዲሰራ ከተመቻቸው የኢኮኖሚ ስርአት ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ገበያ የሚወጣውን የቡና ልክ ለመቆጣጠር አምራች አገሮች የነበራቸው ተቁዋም በመፍረሱ ነው። ቀደም ሲል እነዚህ አገሮች አለም አቀፍ የቡና ስምምነት ወይም «ኢንተርናሽናል ኮፊ አግሪሜንት» በሚለው ተቁዋም አማካኝነት እያንዳንዱ አገር በአመት የሚያቀርበው ኮታ በጋራ ስምምነት ይወስኑ ነበር። ይህ ተቁዋም የዛሬ አስራ ሶስት አመት እንዲፈርስ ተደረገ። እንደቢየትናም ያሉ አዳዲስ የቡና አምራች አገሮች በገበያው ላይ ብቅ አሉ። ነባር አምራች አገሮች ዋጋ እየቀነሰ ሲመጣ ገቢ እንዳይቀነስባቸው ይበልጥ ለመሸጥ ተሩዋሩዋጡ። ጎተራቸውን እያሙዋጠጡ ይሸጡ ጀመር። የዘይት አምራች አገሮች ኦፔክ በተባለው ተቁዋም ተደራጅተው በአለም ደረጃ የቤንዚንን ዋጋ በመጠኑም የሚቆጣጠሩበት አሰራር ሲኖራቸው የድሆች አገሮች ቡና አምራቾች በዚህ መልክ አጥፊ የሆነ ፉክክር ውስጥ ተዘፈቁ። ይህም በመሆኑ ይህንን ንግድ ለሚቆጣጠሩት አራት የምእራብ ግዙፍ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ጨርሶ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ትርፍ የሚያካብቱበት ጎዳና ከፈተላቸው።

ሁለተኛው ጥያቄ ተጠቃሚዎቹ እነማን ናቸው? የሚለው ጥያቄ ነው። የምእራብ አገሮች ሸማቾች ከዚህ ምን ያገኙት ጥቅም አለ? መልሱ ምንም የለም ነው። ቡና ከድሃ አገሮች አምራቾች ተነስቶ እስከ ምእራብ አገሮች የቡና ሸማች እስኪደርስ ድረስ ዋጋ በዋጋ ላይ እየተጨመረ ሂዶ በኪሎ እስከ ሁለት መቶ ሃያ ብር ድረስ ይሸጣል። ከፍ ብለን እንዳልነው የሃገራችን አምራቾች በኪሎ የሚያገኙት ካምስት ብር ወደ ሰማንያ አምስት ሳንቲም ወርዱዋል።

የምእራብ ሸማቾች ግን አሁንም በኪሎ በአማካኝ ሁለት መቶ ሃያ ብር ይከፍላሉ። ከቅናሹ እዚህ ግባ የሚባል ጥቅም አላገኙም። ልዩነቱን እኪሳቸው የሚያደርጉትና ከዚህ የድሃ ገበሬዎ ችን ህይወት በማናጋት ላይ ካለ ኪሳራ በቢልየን የሚቆጠር ዶላር በየአመቱ የሚያካብቱት ድን በር ዘለሎቹ ግዙፍ ኩባንያዎች ናቸው።

ሶስተኛ ጥያቄ ለዚህ የገበያ አቅርቦት መትረፍረፍና ለሚከተለው የዋጋ ማሽቆልቆል ሌሎች ተጠያቂዎች አሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ መንግስታዊ ያልሆ ኑ ድርጅቶች ለዚህ ውድቀት ሁለት ሌሎች ተጠያቂዎች እንዳሉ ይጠቁማሉ። አንደኛ ተጠያ ቂዎች የድሆች አገሮች መንግስታት ራሳቸው ናቸው። ሊከተል ስለሚችለው ችግር ምንም ሳ ይጨነቁ የውጭ ምንዛሪ ሲያባርሩ ትናንሽ ገበሬዎች ከአመት አመት ይበልጥ እንዲያመርቱ ግ ፊት ያደርጋሉ። ሁለተኛ ተጠያቂዎች አይኤምኤፍና የአለም ባንክ ናቸው። ለድሃ አገሮች መ ንግስታት ብድር ለመስጠትና ይህ ብድር ደግሞ ከነወለዱ መከፈሉን ለማረጋገጥ የነዚህ አገሮ ች ልማት በኤክስፖርት ላይ እንዲያተኩር ስለዚህም እንደቡና ያሉ ለኤክስፖርት የሚሆኑ ም ርቶች እንዲያድጉ ግፊት ያደርጋሉ። በዚህ መልክ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቶ የብድራቸው መከ ፈል እንጂ ይህ ሁኔታ በድሃ ገበሬዎች ኑሮ የሚያስከትለው ቀውስ ጉዳያቸውም አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ እንግዲህ አለም አቀፉ ነጻ ገበያ ተብየው ስርአት አለ። አቶ መለስ ብለ ውታል። በአዲስ አበባ ይህንን የቡና ዋጋ ቀውስ አስመልክቶ በያዝነው ሳምንት በተደረገው ጉ ባኤ ሲናገሩ «በአለም ደረጃ ያለው የንግድና የልውውጥ ስርአት ለድሆች አገሮች ሲሆን ሙ ሉ በሙሉ ግፈኛ ስርአት ለመሆኑ ከዚህ ቀውስ ይበልጥ ማረጋገጫ የለም» ሲሉ ተደምጠዋል ።

የዚህ በግሎባላይዜሽን ሳቢያ ግፈኝነቱ የተባባሰው አለም አቀፍ ስርአት አሰራር ለምን ለኛ ለድሆች አገሮች አያመችም። መልሱ በጥቅሉ ሲቀርብ እንደዚህ ነው። ስርአቱ በነጻ ገበያ መርህዎች ላይ የተገነባ ስርአት ነው ተባለ እንጂ በነዚህ መርህዎች ጸንቶ የሚሰራ ስርአት አ ይደለም። ይህም ማለት ለምሳሌ የድሃ አገሮች ምርቶች በበለጸጉት አገሮች ከሚመረቱት ይበ ልጥ ርካሽ ሆነው ከተገኙ በነጻ ገበያ መርህዎች መሰረት ሃብታሞቹ ገበያ ቀርበውና ተወዳድረ ው በቀላሉ መሸጥ ይችሉ ነበር። ይህ እንዳይሆን የኛ ምርቶች በግምሩክ ቀረጥና በሌሎች መሰናክሎች የበለጸጉት አገሮች ገበያ ዝር እንዳይሉ ይደረጋሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው ቀርቶ እህል በበለጸጉት አገሮችና በኛ አገሮች ሲመረት የማምረቻው ዋጋ በኛ አገሮች በጣም ዝቅተኛ ነው። አንድ ኩንታል ስንዴ ለማምረት በአሜሪካና በአውሮፓ አገሮች የሚወጣው ወ ጭ ከኛ አገር ሲነጻጸር ሰማይ ጠቀስ ወጭ ነው። ግን ደግሞ የነዚህ አገሮች እህል ከገበያ ኢ ኮኖሚ መርህዎች ውጭ በመንግስት ድጎማ እየታገዘ በኛ አገሮች በአልባሌ ዋጋ ገበያ እንዲቀ ርብና የሀገሮቻችንን ገበሬዎች ተወዳድሮ እንዲያሸንፍና ህልውናቸውን እንዲያናጋ ይደረጋል። በአጭሩ የነጻ ገበያ ህግጋት ለበለጸጉት አገሮች ሲያመቹ ይከበራሉ። ለነሱ ካላመቹ ደግሞ አ ይን ባወጣ ሁኔታ ይሻራሉ። የስርአቱ ግፈኛነት አንዱ መልኩ ይኸ ነው። ለሁሉም በእኩል አ ይሰራም።

ይህ አይነቱ ግፈኛ አሰራር ለዘመናት የቆየ አፍሪካንም ሆነ ሌሎቹን የደቡብ አገሮች ለድ ቀትና ለሁዋላ ቀርነት የዳረገ አሰራር ነው። አዲስ አይደለም። አዲስ ነገር ቢኖር ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ወዲህ በአለም ደረጃ የተንሰራፋው የግሎባላይዜሽን የኢኮኖሚ ስርአት ይህ የተዛባ አሰራር ይበልጥ እንዲዛባና በቢልየን የሚቆጠሩ የአለም ዜጎችን ከእለት እለት እየከፋ ለሚሄድ ድህነት እየዳረገ የሚሄድበት ሁኔታ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ እየተመቻቸ መሄ ዱ ነው።

መፍትሄውስ ምንድን ነው? ኦክስፋም የተባለው መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ይህንን የቡና ቀውስ አስመልክቶ ባለፈው ሳምንት ከአዲስ አበባ አለም አቀፉዊ ዘመቻ ሲከፍት ይዞ የተነሳ ው መፈክር «ለቡና ተገቢ ዋጋ ይከፈል» የሚል መፈክር ነው። ከዚህ ተነስቶ ለወቅቱ ችግር የሚሰነዝራቸው አራት መፍትሄዎች

1ኛ. በአለም አቀፍ ደረጃ የቡናን ገበያ የሚቆጣጠሩት አራት ግዙፍ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ላይ መንግስታትም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊውን ጫና በማድረግ እነዚህ ኩባንያዎች ለአምራች ገበሬዎች የሚከፍሉትን ዋጋ ከፍ እንዲያደርጉ ማስገደድ

2. በአሁኑ ጊዜ የቡና ምርት ተትረፍርፎ ስለሚገኝ ትርፍ የሆነውን ቡና ማቃጠል

3. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአለም ገበያ ላይ ጥራትና ደረጃ ያልጠበቀ ቡና በሰፊው እየተመረተ በመምጣቱ ጥራትና ደረጃ ያልጠበቀ ቡና ገበያ እንዳይቀርብ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግ

4. የቡና አምራች አገሮች መንግስታት ገበሬዎች ከቡና ማምረቱ ተግባር በተጉዋዳኝ ለምግብ የሚሆን ሰብል የሚያመርቱበት ሁኔታዎች እንዲያመቻቹላቸው አሳስበዋል።

ይህ በአጭር ጊዜ መሰራት አለበት የመባለውን የሚጠቁም ነው። ከዚህ አልፎ ደግሞ ከጥቂት አመታት ወዲህ ለቡና ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በደቡብ አገሮች ለሚመረቱ እቃዎች ይሰራል ተብሎ የታሰበ «ፌይር ትሬድ» ወይም ፍትሃዊ ልውውጥ የሚል ንቅናቄ አለ። የዚህ መሰረተ ሃሳብ የደቡብ አምራቾችን ከበለጸጉት አገሮች ሸማቾች ጋር የሚያገናኙ የሽያጭ መአከሎች በያለበት ማቋቋቁዋምና አሁን በአለም አቀፍ ደረጃ ተደላድሎ ካለው የንግድ አሰራር ውጭ ለደቡብ አገሮች አምራቾች ተገቢ ዋጋ እየከፈሉ አነስተኛ በሆነ ትርፍ ለበለጸጉት አገሮች ሸማቾች ማቅረብ የሚል ሃሳብ ነው። በአሜሪካም ሆነ በአውሮፓ በዚህ መልክ ከደቡብ ሸማቾች በተገቢ ዋጋ እየተገዙ ምርቶች ለበለጸጉት አገሮች ሸማቾች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡባቸው ሱቆች በመስፋፋት ላይ ይገኛሉ።

ይህ የፌይር ትሬድ ንቅናቄ እያደገ የሚሄድ ንቅናቄ ነው። ግን ደግሞ ይህ ብቻ በግሎባላይዜሽንና በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ ስርአት እየተባባሱ ለሄዱት የድሆች አገሮች ችግሮች ዘላቂና አጠቃላይ መፍትሄ አይሆንም። እነዚህ አገሮች ዛሬ የሃገራቸውን ጥቅም ረስተውና ለህዝቦቻቸው ያለባቸውን ሃላፊነት ዘንግተው ለዚህ አለም አቀፍ የግሎባላይዜሽን ስርአት የተንበረከኩ መሪዎቻቸውን አስወግደው በአለም አቀፍ ደረጃ ፍትሃዊ ለሆነ ግሎባላይዜሽን በቆራጥነት የሚቆሙ ህዝባዊና ብሄራዊ ራእይ ያላቸው አመራሮች እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ይህ እስካልሆነና በበለጸጉት አገሮች ተጠንስሶ፣ ለበለጸጉት አገሮች ብቻ ተመቻችቶ በተዋቀረ አለም አቀፍ ስርአት ውስጥ ገብቶ በመዳከር የሃገር ልማትና እድገት እናመጣለን ማለት የማያዋጣ ህልም እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።